# የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና ጤና ክብካቤ

# አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን

## ፕሪከርሰር ኬሚካሎችን ለመቆጣጠር እና በአግባቡ ጥቅም

## ላይ ለማዋል የወጣ  መመሪያ

ህዳር 2006 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## ማውጫ

ገጽ

መግቢያ………………………………………………………………………… 1

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ…………………………………………………………………….. 2

2 ትርጓሜ……………………………………………………………………….. 2

3. ዓላማ…………………………………………………………………………. 3

4. የተፈፃሚነት ወሰን………………………………………………………….... 4

### ክፍል ሁለት
### ስለ ፈቃድና የፈቃድ አሰጣጥ ስርዓት

5. የፈቃድ አስፈላጊነት……………………………………………………….... 4

### ክፍል ሦስት

### የፕሪከርሰር ኬሚካል ማስመጣት፣ መላክና ማስተላለፍ

6. የማስመጣት ወይም የመላክ ልዩ ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ……………. 5

7. የማስመጣት ወይም የመላክ ልዩ ፈቃድ ስለመስጠት…………………………………… 6

8. የማስመጣት ልዩ ፈቃድ ኮፒዎች ስርጭት…………………………………………... 7

9. ስለ ልዩ ፈቃድ የአገልግሎት ጊዜ ገደብ…………………………………………… 7

10. ፕሪከርሰር ኬሚካልን ከመግቢያና መውጪያ በር ስለማስለቀቅ……………………… 8

### ክፍል አራት
### ሪከርድ አያያዝ እና ሪፖርት አቀራረብ

11. አጠቃላይ……………………………………………………………………… 9

12. ስለ መረጃ አያያዝ…………………………………………. …………………….. 9

13. ስለ ሪፖርት አቀራረብ…………………………………………………………..... 10

### ክፍል አምስት
### ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

14. ስለ አያያዝ ………………………………………………………………………. 10

15. ስለ አወጋገድ…………………………………………………………………. 10

16. ስለ ልዩ የማስገቢያ ፈቃዱ የሚያበቃበት ጊዜ እና ማሳደስ………………………………… 11
17. እገዳና ስረዛ…………………………………………………………………… 11
18. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች………………………………………………… 11
19. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ …………………………………………………...…........ 11
20. እዝል ……………………………………………………………………………… 12-16

## መግቢያ

ከፕሪከርሰር ኬሚካሎች ሕገወጥ ዝውውርና አጠቃቀም የተነሣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በሕብረተሰቡ ጤና፣ ማኀበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ዘርፍ ላይ የሚፈጥሩት ተፅዕኖ እየጨመረ በመምጣቱ፤

ከፕሪከርሰር ኬሚካሎች የሚዘጋጁ ንጥረ ነገሮች ህገ ወጥ ዝውውር የተነሳ የተቀናጀና ሁሉን አቀፍ የሆነ የፕሪከርሰር ኬሚካሎች ቁጥጥር መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

ናርኮቲክና ሣይኮትሮፒክ ንጥረ ነገሮች የሚሰሩባቸውን ፕሪከርሰር ኬሚካሎች ያለምንም ቁጥጥር በብዛትና በቀላሉ ከተገኙ ለሕገወጥ አጠቃቀም ስለሚዳረጉ እንዲሁም ከፕሪከርሰር ኬሚካሎች የሚቀመሙ ዝግጅቶች በስፋት ለሕክምና አገልግሎት የሚውሉና በቀላል ዘዴ ወደ ተሰራበት ንጥረ ነገሮች መለወጥ በመቻሉ ከሚያስከትሉት አደጋ አስፈላጊውን ቁጥጥር ማድረግ በማስፈለጉ።

ፕሪከርሰር ኬሚካሎችን መቆጣጠር በአለም አቀፍ ደረጃ የናርኮቲክና ሣይኮትሮፒክ መድኃኒቶችን ለመቆጣጠር ከወጡ ስልቶች መካከል አንዱ በመሆኑ።

የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 661/2002 አንቀጽ 55(3) መሰረት ይህ መመሪያ ወጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## አጠቃላይ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "ፕሪከርሰር ኬሚካሎችን ለመቆጣጠር እና በአግባቡ ጥቅም ላይ ለማዋል የወጣ መመሪያ ቁጥር 18/2006 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

በአዋጅ ቁጥር 661/2002 የተሰጠው ትርጉም እንደተጠበቀ ሆኖ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

1) "ፕሪከርሰር ኬሚካል" ማለት ኢትዮጵያ በተቀበለችው የተባበሩት መንግሥታት የናርኮቲክ ወይም የሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶች ህገ ወጥ ዝውውር ለመግታት በወጣው ስምምነት መሠረት ቁጥጥር የሚደረግባቸው ኬሚካሎች፣ ንጥረ ነገር ወይም የንጥረ ነገሮች ውህድ ሲሆን ባለስልጣኑ ፕሪከርሰር ኬሚካል ብሎ የሚሰይመውንም ይጨምራል፤

2) "ውህድ" ማለት በአለም አቀፍ ደረጃ የፕሪከርሰር ኬሚካል ለመቆጣጠር በወጣው ሠንጠረዥ (I) እና (II) የሚገኙት ኬሚካሎች እርስ በርሳቸውም ሆነ ከሌሎች ኬሚካሎች ጋር ተደባልቀው የሚገኙበትና ናርኮቲክና ሣይኮትሮፒክ መድኃኒቶችን ሕገወጥ በሆነ መልክ ለማምረት፣ ለመቀመም ወይም ለማጣራት ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉትን ኬሚካሎችም ያካትታል፡፡

3) "ሠንጠረዥ (I) እና (II) ኬሚካሎች" ማለት የተባበሩት መንግሥታት እ.ኤ.አ. በ1988 የናርኮቲክና ሣይኮትሮፒክ መድኃኒቶችን ሕገወጥ ዝውውር ለመግታት ባወጣው ስምምነት መሠረት በዕዝል 1 የተገለፁትና ቁጥጥር የሚደረግባቸው ኬሚካሎች ናቸው፡፡

4) “ማምረት” ማለት ፕሪከርሰር ኬሚካሎችን ለማግኘት የሚደረግ ሂደት ሆኖ መቀመም ወይም ፊዚካላዊ ወይም ኬሚካላዊ በሆነ መንገድ የኬሚካሎችን ባሕሪ መቀየር ወይም ፕሪከርሰር ኬሚካል በመጠቀም ማምረት ወይም ፕሪከርሰር ኬሚካሎች የሚገኙባቸውን ተክሎች ማብቀል፣ ማባዛትና መሰብሰብን ይጨምራል፡፡

5) “ማጣራት” ማለት ፕሪከርሰር ኬሚካሎችን ፊዚካላዊ ወይም ኬሚካላዊ በሆነ መንገድ ከተለያዩ ዝግጅቶች ለመለየት የሚደረጉ ሂደት ነው፡፡

6) “ማስተላለፍ” ማለት በጉምሩክ የቁጥጥር ህግ ሥርዓት አማካኝነት ከአንዱ የመጓጓዣ ዓይነት ወደ ሌላው መጓጓዣ ዕቃዎችን የማስተላለፍ የአሰራር ቅደም ተከተል ነው፡፡

7) “ሀርሞናይዝድ ሲስተም ኮድ” ማለት በአለም አቀፍ የጉምሩክ ድርጅት መለያ መሠረት ዕቃዎች የየራሳቸው የመለያ ቁጥር የሚሰጥበት የአሰራር ሥርዓት ነው፡፡

8) “የማስገቢያ ፈቃድ” ማለት ፕሪከርሰር ኬሚካሎችን ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ከባለስልጣኑ የሚሰጥ ልዩ ፈቃድ ነው፡፡

9) “የመላኪያ ፈቃድ” ማለት ፕሪከርሰር ኬሚካሎችን ወደ ውጪ ሀገር ለመላክ ከባለስልጣኑ የሚሰጥ ልዩ ፈቃድ ነው፡፡

10) “ባለስልጣን” ማለት የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ነው፡፡

11) “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት ስልጣን የተሰጠው አካል ነው፡፡

## 3. ዓላማ

የናርኮቲክ መድኃኒትና ሣይኮትሮፒክ ንጥረ ነገርን ለማምረት እና ለማጣራት የሚጠቅሙ ፕሪከርሰር ኬሚካሎችን ማምረት፣ መቀመም፣ ማዘጋጀት፣ ማከማቸት፣ ማስመጣት፣ መላክ፣ ገበያ ላይ ማዋልና ማጓጓዝን በተመለከተ ለመቆጣጠርና በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ለማድረግ ነው፡፡

4. **የተፈፃሚነት ወሰን**

የዚህ መመሪያ ተፈፃሚነት ፕሪከርሰር ኬሚካሎችን በማምረት፣ በማስመጣት፣ በመላክ፣ በጅምላ በማከፋፋል፣ በማከማቸት፣ በማጓጓዝ፣ገበያ ላይ በማዋል ወይም በመያዝ ሂደት ላይ በተሰማሩ ተቋማት ወይም ሰዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለ ፈቃድና የፈቃድ አሰጣጥ ስርዓት

5. **የፈቃድ አስፈላጊነት**

1) ማንኛውም ድርጅት ከባለስልጣኑ ልዩ ፈቃድ ሳያገኝ በባለስልጣኑ በፕሪከርሰር ኬሚካልነት የተፈረጁ ኬሚካሎችን እንደ ጥሬ እቃነት መጠቀም፣ ማምረት፣ ማስመጣት፣ መላክ፣ በጅምላ ማከፋፈል፣ ማከማቸት ማጓጓዝ ወይም መያዝ አይችልም፡፡

2) ፕሪከርሰር ኬሚካሎችን ለማምረት፣ ለማዘጋጀት፣ ለመለወጥ፣ ለማከማቸት፣ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት፣ ወደ ውጪ ለመላክ ወይም በማንኛውም ዓይነት ንግድ ውስጥ ለመሣተፍ በመጀመሪያ ከባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፡፡

3) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) እንደተጠበቀ ሆኖ እንደ ጥሬ እቃነት ለኢንዱስትሪ፣ለማስተማሪያ እና ለምርምር በሚጠቀሙ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ሰርቴፊኬት ሳያስፈልጋቸው ልዩ ፍቃድ ማግኘት ይችላሉ፡፡

4) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (3) እንደተጠበቀ ሆኖ ልዩ ፈቃድ ለማግኘት የሚከተሉትን መረጃዎች ማቅረብ አለበት፡-

   ሀ/የአመልካቹ ሙሉ ስም፣ ሙያ፣ ዜግነት፣

   ለ/የድርጅቱን ስምና አድራሻ፣

ሐ/ የንግድ ፈቃድ፣

መ/ የፕሪከርሰር ኬሚካሉን ስም፣ ዓይነትና ጥንካሬ እንዲሁም ፕሪከርሰር ኬሚካሉ የሚውልበት ዓላማ ማካተት አለበት፡፡

5) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (4) መሰረት ለባለስልጣኑ የቀረበውን ማመልከቻ ተስተካክሎ በድጋሚ እንዲቀርብ ለመመለስ፣ የተጠየቀውን ፕሪከርሰር ኬሚካል መጠን ለመቀነስ፣ ክብደት ለማሻሻል ወይም አስፈላጊ ያልሆኑትን ከዝርዝር የማውጣት ሥልጣንና ኃላፊነት አለው፡፡

## ክፍል ሦስት

## የፕሪከርሰር ኬሚካል ማስመጣት መላክና የልዩ ፈቃድ አገልግሎት ጊዜ ገደብ

### 6. የማስመጣት ወይም የመላክ ልዩ ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ

1) ማንኛውም ሰው የፕሪከርሰር ኬሚካልን ለማስመጣት ወይም ለመላክ የሚያስችለውን ልዩ ፈቃድ ከባለስልጣኑ ለማግኘት ከማመልከቻው ጋር የሚከተሉትን መረጃዎች ማቅረብ አለበት፡-

ሀ) በሀርሞናይዝድ ሲስተም ኮድ መሠረት የፕሪከርሰር ኬሚካሉ ስም ወይም የተሰራበት ንጥረ ነገር፣

ለ) በጨው መልክ ከሆነ የጨዉ መለያ ስም፣

ሐ) ዝግጅት ወይም ውህድ ከሆነ በውስጡ የተካተቱ የፕሪከርሰር ኬሚካል ዓይነቶች በዝርዝር መጠቀስ አለበት፣

መ) የፕሪከርሰሩ ኬሚካል መጠንና መለኪያ እንዲሁም ዝግጅት ወይም ውህድ ከሆነና ከአንድ በላይ ፕሪከርሰር ኬሚካሎች የያዘ ከሆነ የእያንዳንዱ መጠንና መለኪያ መገለፅ አለበት፣

ሠ) የአስመጪዉና የላኪው ድርጅት ስምና አድራሻ፣

ረ) የማጓጓዣ ዓይነትና ለማስተላለፊያነት የሚጠቀምበት ሀገር ካለ መጠቀስ አለበት፣

ሰ) የፕሪከርሰር ኬሚካሉ ለምን አገልግሎት እንደሚውል መገለፅ አለበት፡፡

ሸ) ማመልከቻው በድርጅቱ ኃላፊ ወይም ሕጋዊ ተወካይ ተፈርሞ ማህተም ያለው መሆን አለበት፣

ቀ) የሚገቡት ፕሪከርሰር ኬሚካሎች አይነት ከአንድ በላይ ከሆኑ በማመልከቻው ላይ መገለጽ አለበት፣

በ) በዚህ መመሪያ እዝል 7 ከተቀመጡት ፕሪከርሰር ኬሚካሎች ውጪ ማስገባት አይቻልም፡፡

2) ባለስልጣኑ እንደ አግባቡ የቀረበውን ማመልከቻ ተስተካክሎ በድጋሚ እንዲቀርብ ለመመለስ፣ የተጠየቀውን ፕሪከርሰር ኬሚካል መጠን ለመቀነስ፣ ክብደት ለማሻሻል ወይም አስፈላጊ ያልሆኑትን ከዝርዝር የማውጣት ሥልጣንና ኃላፊነት አለው፡፡

7. **የማስመጣት ወይም የመላክ ልዩ ፈቃድ ስለመስጠት**

1) ባለስልጣኑ በዚህ መመሪያ አንቀጽ (7) ስር የተጠቀሱትን መስፈርቶች መሟላታቸውን ሲያረጋግጥ የማስገቢያ ወይም የመላኪያ ልዩ ፈቃድ ይሰጣል፡፡ ልዩ ፈቃዱም የሚከተሉትን መረጃዎች ይይዛል፡-

ሀ) የፈቃድ ቁጥር፣

ለ) የድርጅቱ ስምና ሙሉ አድራሻ፣

ሐ) የፕሪከርሰር ኬሚካሉ ስም፣ ጥንካሬ፣ ዓይነት፣ መጠንና መለኪያ፣

መ) ፈቃዱ የተሰጠበት ቀን፣

ሠ) ፈቃዱ የሚያበቃበትን ጊዜ፣

ረ) የፈቃድ ሰጪው ኃላፊ ሙሉ ስም፣ ፊርማና ማህተም፡፡

2) የፐሪከርሰር ኬሚካል የማስመጣት ወይም የመላክ ልዩ ፍቃድ ማመልከቻው በሁለት የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ማግኘት አለበት፡፡

3) ባለስልጣኑ ፐሪከርሰር ኬሚካልን ከሀገር ውስጥ እንዲወጣ ልዩ ፈቃድ ሊሰጥ የሚችለው ከተቀባይ ሀገር ካለው ተቆጣጣሪ አካል የማስገቢያ ፈቃድ መኖሩን ሲያረጋግጥ ነው፡፡

## 8. የማስመጣት ልዩ ፈቃድ ኮፒዎች ስርጭት

ፐሪከርሰር ኬሚካል ለማስመጣት የሚሰጠው ልዩ ፍቃድ በአራት ቅጂ የሚዘጋጅ ሆኖ፡-

1) ዋናው ቅጂ ለአስመጪው የሚሰጥ ሆኖ አስመጪው ቅጅውን ለላኪው ድርጅት መላክ አለበት፡፡
2) ባለስልጣኑ ሁለተኛውን ቅጂ ላኪው ድርጅት ለሚገኝበት አገር ተቆጣጣሪ አካል ይልካል፡፡
3) ባለስልጣኑ ሶስተኛውን ቅጂ ፐሪከርሰር ኬሚካል በሚገባበት የመውጫና መግቢያ በር ለሚገኝ ለባለስልጣኑ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ለክትትል ይላካል፡፡
4) አራተኛ ቅጂ ለባለስልጣኑ ቀሪ ይሆናል፡፡

## 9. ስለ ልዩ ፈቃድ የአገልግሎት ጊዜ ገደብ

1) ፐሪከርሰር ኬሚካል ለማስመጣት ወይም ለመላክ የሚሰጥ ልዩ ፈቃድ የሚያገለግለው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በዘጠና ቀናት ውስጥ አንድ ጊዜ ለማስመጣት ወይም ለመላክ ብቻ ይሆናል፡፡
2) የተሰጠው ልዩ ፈቃድ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጥቅም ላይ ሳይውል ሲቀርና ለባለስልጣኑ ሲመለስ ወይም የተሰጠው ልዩ ፈቃድ የጠፋ ከሆነ መጥፋቱን ህጋዊ ከሆነ አካል መረጃ ሲቀርብ የተሰጠው ልዩ ፈቃድ ተሰርዞ በምትኩ አዲስ ልዩ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡

## 10. ፕሪከርሰር ኬሚካልን ከመግቢያና መውጫ በር ስለማስለቀቅ

1) ማንኛውም ሰው ፕሪከርሰር ኬሚካል ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት፡-

   ሀ/ በባለስልጣኑ የተሰጠ ልዩ የማስገቢያ ፈቃድ፣

   ለ/ ፕሪከርሰር ኬሚካል የሚመጣው በአየር መጓጓዣ ሆኖ ለብቻው የታሸገ፣እና

   ሐ/ ለዚህ አላማ ብቻ የተዘጋጀ ኢንቮይስ፣

   ማሟላት አለበት፡፡

2) ማንኛውም ሰው ፕሪከርሰር ኬሚካል ወደ ሀገር ውስጥ ሲያስገባ ከተሰጠው ልዩ ፈቃድ የመጠን፣ የጥንካሬ እና የስም ለውጥ መኖር የለበትም፡፡

3) ማንኛውም ሰው ፕሪከርሰር ኬሚካል ከመውጫና መግቢያ በር ላይ ለማስለቀቅ የሚከተሉትን ሰነዶች ከማመልከቻው ጋር አያይዞ ማቅረብ አለበት፡-

   ሀ) የምዝገባ ምስክር ወረቀት ፣

   ለ) ለእያንዳንዱ መለያ ቁጥር የተሰጠው የይዘት ምስክር ወረቀት ዋና ወይም ቅጅውን ፣

   ሐ) የስሪት አገር ማረጋገጫ ሰርተፊኬት፣

   መ) የእቃ ዝርዝር መግለጫ ሰነድ፣

   ሠ) ቢል ኦፍ ሎዲንግ ወይም ኤርዌይ ቢል፣

   ረ/) ኢንቮይስ ፣ እና

   ሰ) የቅድመ መግቢያ ፈቃድ ሰርተፊኬት።

4) ባለስልጣኑ በመውጫና መግቢያ በር ላይ የቀረበለትን ሰነድ ትክክለኛነት በማረጋገጥ የመልቀቂያ ፈቃድ ይሰጣል፡፡ የመልቀቂያ ፈቃድ ኮፒም ለገቢዎችና የጉምሩክ ባለስልጣን እና ለአስመጪው ወይም ለላኪው ድርጅት ይሰጣል፡፡

## ክፍል አራት

## ሪከርድ አያያዝ እና ሪፖርት አቀራረብ

## 11. አጠቃላይ

1) ማንኛውም የፕሪከርሰር ኬሚካል ያመረተ፣ ያስመጣ፣ የላከ፣ ወይም ያከፋፈለ ሰው የዕለት የሥራ ክንውን መረጃ የመያዝና ባለስልጣኑ በሚያስቀምጠው ጊዜ ሰሌዳ ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡ መረጃዎችን ቢያንስ ለሁለት ዓመት መያዝ ይኖርበታል፡፡

2) ማንኛውም ሰው ያስገባውን ፕሪከርሰር ኬሚካል ሪፖርት ሳያደርግ ሌላ ልዩ ፈቃድ ማግኘት አይችልም፡፡

## 12. ስለ መረጃ አያያዝ

1) ማንኛውም የፕሪከርሰር ኬሚካል አምራች፣ አስመጪ፣ ላኪ ወይም ጅምላ አከፋፋይ ድርጅት የሚከተሉትን መረጃዎች አሟልቶ መያዝ አለበት፡-

   ሀ) ያስመጣውን እና  የላከውን መጠን በቅፅ PR/01/C፡፡

   ለ) ያመረተውን፣ ያዘጋጀውን፣ የቀመመውን መጠን በቅፅ PR/01/F፡፡

   ሐ) በሀገር ውስጥ ገበያ የተሸጠ፣ የተከፋፈለ፣ ጥቅም ላይ የዋለ የፕሪከርሰር ኬሚካል መጠን በቅፅ PR/02/C አሟልቶ መያዝ አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስር የተጠቀሱት መረጃዎች ቢያንስ የሚከተሉትን መረጃዎች ማካተት አለበት፡-

   ሀ) የንግድ ልውውጡ የተካሄደበትን ጊዜ፣

   ለ) የተቋሙ ስምና ሙሉ አድራሻ፣

   ሐ) የፕሪከርሰር ኬሚካሉ ስም፣ መጠን፣ ጥንካሬ፣ መለኪያ እና የዝግጅት ዓይነት ማካተት አለበት፡፡

13. ስለ ሪፖርት አቀራረብ

1) ማንኛውም የፕሪከርሰር ኬሚካል አምራች፣ አስመጪ፣ ላኪ ወይም ጅምላ አከፋፋይ ያስመጣውን፣ የላካውን ወይም ያከፋፈለውን የፕሪከርሰር ኬሚካል መጠን በየሩብ አመቱ መጨረሻ ለባለስልጣኑ በቅፅ PR/01/C እና PR/02/C ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡
2) ማንኛውም የፕሪከርሰር ኬሚካል አምራች፣ አስመጪ ወይም ላኪ ያመረታቸውን፣ ያስመጣቸውን፣ ያከፋፈላቸውን እንዲሁም የተጠቀመውን የፕሪከርሰር ኬሚካል መጠን በየአመቱ መጨረሻ ለባለስልጣኑ በቅፅ PR/03/C ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

14. ስለ አያያዝ

የማንኛውም የፕሪከርሰር ኬሚካል ኢንቮይስ፣ የሪከርድ ቅጽ እና መዛግብት ቁልፍ ባለው የብረት ሣጥን ወይም በተለየ ክፍል ውስጥ ማስቀመጥና ቁልፉም በተፈቀደለት ባለሙያ ብቻ እንዲያዝ መደረግ አለበት፡፡

15. ስለ አወጋገድ

1) ማንኛውም ሰው የአገልግሎት ጊዜ በማብቃቱ ወይም በመበላሸቱ ምክንያት ጥቅም ላይ የማይውል የፕሪከርሰር ኬሚካል እንዲወገድለት አግባብ ላለው ተቆጣጣሪ አካል ማመልከት ይኖርበታል፡፡ አግባብ ላለው ተቆጣጣሪ አካል መወገዱን በማረጋገጥ ስለመወገዱ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡
2) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ አወጋገዱ የመድኃኒት ቆሻሻ አስተዳደር እና አወጋገድ መመሪያ ቁጥር 2/2004 መሰረት ያሆናል፡፡
3) በሕገወጥ ዝውውር፣ ምርት ወይም ገበያ ውስጥ የተገኙ ወይም የተያዙ ፕሪከርሰር ኬሚካል በባለስልጣኑ አግባብ ባለው መመሪያ መሰረት እንዲወገድ ያደርጋል፡፡

16. ስለ ልዩ የማስገቢያ ፈቃዱ የሚያበቃበት ጊዜ እና ማሳደስ

1) አንድ የፕሪከርሰር ኬሚካል ማስገቢያ ልዩ ፈቃድ ከዘጠና ቀናት በላይ ጥቅም ላይ አይውልም፡፡
2) ማንኛውም ድርጅት ለአንድ ጊዜ ፕሪከርሰር ኬሚካል ለማስመጣት የወሰደው ልዩ የማስገቢያ ፈቃድ በተለያዩ ምክንያት ጊዜ ካለፈበት እንደገና ለማሳደስ መመለስ አለበት፡፡

17. እገዳና ስረዛ

ማንኛውም ስራውን በራሱ ፈቃድ ያቋረጠ፣ እገዳ ወይም ስረዛ የተጣለበት ድርጅት በእጁ ያሉ አገልግሎት ላይ መዋል የሚችሉ ፕሪከርሰር ኬሚካልን ባለስልጣኑን በማስፈቀድ ህጋዊ ፈቃድ ላላቸው ድርጅቶች በተሰጠው ጊዜ ገደብ መሸጥ፣ ማከፋፈል ወይም ማስተላለፍ አለበት፡፡

18. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ ወይም ሰርኩላር ደብዳቤ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተመለከቱ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

19 መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከሕዳር 1 2006 ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**የሁሉ ደነቀው**
**የኢትዮጵያ የምግብ የመድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን**
**ዋና ዳይሬክተር**

Annex 1

Form PR/01/c

Quarterly Statistics of imports Precursor chemicals

Name of Reporting Organization ____________________________

Address: Region ________________ City/Town ________________

P.O. Box ______________ Tel. _____________________

These statistics relates to the quarter of the calendar year ________________

| Ser. No. | precursor chemicals | Dosage Form | Strength | | Quantity | | Stock | Import | Remark |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | At the beginning of the quarter | Manufactured | Distributed | at the end of the quarter | Import permit no. | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |

Remark: - Report on all controlled precursor chemical is required quarterly.

Annex 2

Form PR/01/F

Quarterly Statistics of manufactured Precursor chemicals

Name of Reporting Organization ____________________________

Address: Region ________________ City/Town ________________

P.O. Box ______________ Tel. _____________________

These statistics relates to the quarter of the calendar year ________________

| Ser. No. | precursor chemicals | Dosage Form material | Strength | Unit | | Quantity | | Stock at the end of the quarter | Import permit no. | Remark |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | At the beginning of the quarter | Manufactured | Distributed | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |

Remark: - Report on all controlled precursor chemical is required quarterly.

Annex 3

Form PR/02/c

Quarterly Statistics distributed/consumed of Precursor chemicals

Name of Reporting Organization ______________________________

Address: Region _________________ City/Town _________________

P.O. Box _______________ Tel. ______________________

These statistics relates to the calendar year

| Ser. No. | precursor chemicals | Dosage Form | Strength | Date of issue | Issued or Consumed by | Unit of issue | Quantity Issued Consumed | Issuing transfer voucher No. | Remark |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |

Remark: - Report on all controlled precursor chemical is required quarterly.

Annex 4

Form PR/01/c

# Annual Statistics of Precursor chemicals

Name of Reporting Organization ____________________________

Address: Region ________________ City/Town ________________

P.O. Box ______________ Tel. _____________________

These statistics relates to the____________quarter of the calendar year ________________

| Ser. No. | precursor chemicals | Dosage Form | Strength | Balance at the beginning of the year | Quantity | | Consumption During the Year | Balance at the end of the year | Remark |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | Imported | Locally purchased | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |

Remark: - Report on all controlled precursor chemical is required quarterly.

Annex 5

Form PR/02/c

# Annual Statistics of Precursor chemicals

Name of Reporting Organization ____________________________

Address: Region ________________ City/Town ________________

P.O. Box ______________ Tel. _____________________

These statistics relates to the____________quarter of the calendar year ________________

| Ser. No. | precursor chemicals | Dosage Form material | Strength | Balance at the beginning of the year | Quantity | | Consumption During the Year | Balance at the end of the year | Remark |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | Exported | Locally purchased | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |

Remark: - Report on all controlled precursor chemical is required quarterly.